ጉባዔ ዐሥራ አንድ።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ዘእምነቤሁ ኵሉ ሀብት ሠናይ።

አሪት ከሱ የተገኘች የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፤

ወኵሉ ፍት ፍጹም።

ልጅነት ከእሱ የተገኘች የእግዚአብሔር አብሕያው የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ አንድም ኵሉ ሀብት ሠናይ፤ አእምሮ ጠባይዕ ከእሱ የተገኘ፣ ወኵሉ ፍት ፍጹም፤ ልጅነት ከእሱ የተገኘ፤ ሀብትኬ ሠናይ መንፈስ ቅዱስ እንዲል። አንድም ኵሉ ሀብት ሠናይ፤አሪት ከእሱ የተገኘች ወትዕዛዛኒ ጽድቅ እንዲል። ወኵሉ ፍት ፍጹም፤ወንጌል ከእሱ የተገኘች አርዑትየኒ ሠናይ እንዲል። አንድም ኵሉ ሀብት ሠናይ፤ ሥጋወ ደሙ ከእሱ የተገኘ። ወኵሉ ፍት ፍጹም፤ ተአምራት ከእሱ የተገኘ፤አንድም ኵሉ ሀብት ሠናይ፤ ኻያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ከእሱ የተገኙ። ወኵሉ ፍት ፍጹም፤ ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መንፈሳዊ ከእሱ የተገኘ የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፤

ኮነ ለብአ።

ፍጹም ሰው ሆነ።

Scanned by CamScanner

ወኵሎ ሕገ ሰብእ ፈጸመ ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ፡፡

ከኀጢአት ብቻ በቀር የሰውነትን ሥራ ሠራ፤ አንድም ሕግ ጠባይዐዊን ሕግ መጽሐፋዊን ፈጸመ፡፡ ሕግ ጠባይዐዊ የተፈጥሮ ሕግ ነው አምላክ ነኝና ዕለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ ሳይል ሕገ ተፈጥሮን ሳያፋልስ ልማደ ሕፃናትን ሳይጥስ እንደ ሕፃናት እያለቀሰ እያነጠሰ እየታዘዘ በየጥቂቱ ማደግ ነው፤ በበሕቅ ልሕቀ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ እንዲል፡፡ ሕግ መጽሐፋዊ ሕገ ኦሪትን መፈጸም ነው፡፡

ወተምህረ ሕገ ዕብራውያን፡፡

የዕብራውያንን ሕግ ተማረ፡፡ በስምንት ቀን ቤተ ግዝረት፣ በአርባ ቀን ዕጕለ ርግብ፣ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መግባት ነው፡፡ አንድም የዕብራውያንን የቀለም ትምህርት ተማረ፡፡ ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ጌታ ለአቅመ ትምህርት ሲደርስ እመቤታችን ወስዳ ለመምህረ ኦሪት ለገማልያል አስተምርልኝ ብላ ሰጠችው እሱም ተቀብሎ አሌፍ በል አለው አሌፍ አለ፤ ቤት በል አለው ምንት ትርጓሜሁ ለአሌፍ የዚህን ትርጓሜ ሳትነግረኝ ነውን አለው ብላቴና የነገሩትን ይቀበላል እንጂ እንዲህ ይመልሳል ብሎ አድንቆ አምላክነቱን አውቆ ትቶታል፡፡ ከሌላ መምህር ወስዳ አስተምርልኝ ብላ ሰጠችው ጸሐፊ ነው ለተግባሩ ከቤት ገብቶ ሳለ ጥቁሩን ቀለም ከቀዩ ቀለም ደባለቀበት ተበሳጭቶ ዝንቱ ወልደ መበለት አማሰነ ቀለምየ ብሎ ፊቱ በጥፊ መታው፤ ለይተህ ስጠኝ ይባላል እንጂ ለምን ትመታኛለህ? አለው፤ ከቀደመው ያሁኑ ይባስ ብሎ ገሠጸው፤ በቁጣ ለይተህ ስጠኝ አለው ለይቶ ሰጥቶታል፤ በዚህ አድንቀዋል፡፡ አንድም ምንጣፍ መሥራት፣ ልብስ ስፌት፣ ቀለም ማግባት ተማረ፡፡ አንዲት ሴት መጥታ ልብሴን ቀለም አግባልኝ አለችው አግብቶ ሰጣት፤ አላማረኝም አለችው እንደ ቀድሞ አድርጎ ለይቶ ሰጥቷታል፤ አንድም አንድ ሴት ልብስ ይዛ መጥታ ስፋልኝ አለችው ሰፍቶ ሰጣት ዋጋ አላወጣልኝም አለችው እንደ ቀድሞ ሥረወጥ አድርጎ ሰጣት፤ በዚህ አድንቀው አምላክነቱን ተረድተዋል፡፡

እምኀበ ዮሐንስ ተጠምቀ፡፡

በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ፡፡

በውስተ ገዳም ተመከረ፡፡

በገዳመ ቆሮንቶስ በሦስቱ አርእስተ ኀጣውእ ተፈተነ፡፡

ርኅበ ወጸምአ፡፡

ተራበ ተጠማ፡፡

ወተአምራተ ገብረ በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ መጠወ ነፍሶ ለሞት፡፡

ሰውነቱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ በሰጠባት በዚያች ሌሊት ተአምራት አደረገ፡፡ በቅዳሴው ሁሉ ተአምራት የሚለው አምስት እንጀራ አበርክቶ ለአምስት ሺ ሰው መመገቡን ነው፡፡

አመረ ለአርዳኢሁ በብዙኅ ትእምርት፡፡

ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ ምልክትን ነገራቸው፡፡ ትእምርተ ሲል ነው፤ በ በግዕዝ ቦታ የገባ ነው፤ ቀስተ ዮናታን ኢተቀብዐት በቅብዕ ዘእንበለ በደመ ኀያላን አንተሰ ኢቀባዕከኒ ርእስየ በዘይት ኦሪት ወነቢያት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ ለምሁራነ ልብ በጥበብ እንዲል፡፡

በእንተ ሕማሙ፡፡

ብዙ ጸዋትወ መከራ ስለ መቀበሉ፤

ወስቅለቱ፡፡

በመስቀል ላይ ስለ መሰቀሉ

ወሞቱ፡፡

ስለ መሞቱ፤

ወትንሣኤሁ በሣልስት ዕለት፡፡

በከርሠ መቃብር ሦስት መዐልት ሦስት ሌሊት አድሮ ሞትን ድል አድርጎ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ብርሃነ መለኮቱን ተዋሕዶ በኃይሉና በሥልጣኑ ስለመነሣቱ ነገራቸው፡፡ አንድም አመረ ለአርዳኢሁ በብዙኅ ትእምርት፤ በብዙ ትእምርተ ቃል በብዙ ትእምርተ ፈትቶ ነገራቸው፡፡ ትእምርተ ፈትቶ ዐሥራ ሦስት አድርጎ በመፈተት፤ ትእምርተ ቃል ናሁ ነዐርግ ኢየሩሳሌም ወይእኅዝዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው[120] እያለ ነገራቸው፡፡ በእንተ ሕማሙ የሕማሙን ነገር፤

120 ማቴዎስ ፲፮ ፡ ፳፩ ፣ ፳፮፡፪

ወስቅለቱ የመሰቀሉን ነገር፤ ወሞቱ የሞቱን ነገር፤ ወትንሣኤሁ በሣልስት ዕለት የትንሣኤውን ነገር ነገራቸው::

በሥጋ ወነፍስ ዐፅም ወደም በከመ ኮነ ትካት እንዘ ሀለዉ ምስሌሁ አርዳኢሁ በየማኑ ወበጸጋሙ::

ደቀ መዛሙርቱ ከሱ ጋራ በቀኝ በግራ ሳሉ ቀድሞ እንደነበረው ሆኖ እንደሚነሣ ነገራቸው:: በሥጋ ወነፍስ ዐፅም ወደም አለ ተለውጦ ተነሣ የሚሉ መናፍቃን አሉና:: አንድም አንድ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ከሱ ጋራ በቀኝ በግራ ሳሉ ነገራቸው::

ወምስሌሆሙ ኍሉቅ ዝኩ ዘፍጥረቱ ክርዳድ ዘምስለ ሥርናይ ድሙር ይሁዳ ዘአግብኦ::

ኍልቁ ቢል ቁጥሩ ኍሉቅ ያለ እንደ ሆነ ከነሱ ጋራ የተቆጠረ ኀጥእ የኀጥእ ልጅ ይሁዳ ከሱ ጋራ ሳለ ነገራቸው:: ይህስ እንደምንድነው ቢሉ ነቢዩ ዕንባቆም ነው ለማስተማር ሲሄድ ብዙ ሰዎች ካሉበት ደረሰ፤ እነዚያ አክብረው ተቀብለው ሲሸኙት የይሁዳ አባት በትዕቢት ከደንጊያ ላይ ተቀምጦ አይቶታል:: ዕብን ላዕለ ዕብን ነቢሮ ብሎ ተናግሮት ሄደ፤ ማታ አስተምሮ ሲመለስ አገኘው እንዳይነሣ ኮርቶ ዝም ብሎ እንዳይቀመጥ ፈርቶ እንደ ጧቱ አንድ ነገር ይናገረኛል ብሎ ያላየ መስሎ በልብሱ ተሸፋፍኖ ተኛ፤ ነቢዩም ከዚህ የሚወለደው ዘአቡሁ ዕልገቱ አባቱን የሚሰልብ፤ ወዘእሙ ብእሲቱ እናቱን የሚያገባ፤ ወዘእግዚኡ ሤጡ ጌታውን የሚሸጥ ነው ብሎ ትንቢት ተናግሮበት ሄደ:: የይሁዳ አባትም ማታ ከቤት ገብቶ ሚስቱን ዛሬ ያ ነቢየ እግዚአብሔር ለምን አላከበርከኝም ብሎ እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረብኝ አላት፤ አንተስ በጎ አድርገሃል? ታላቅ ሰው ሲመጣ ተቀምጦ ማየት ይገባልን ምነው እንደ ሌሎቹ ብታከብረው ምን አለበት ብለዋለች፤ ተይው እባክሽ የሆነውን ያልሆነውን ቢቀባጥር መቼስ ካልተገናኘን ይህ አይደረግ ከመገናኘት ተከልክለን እንኖራለን አላት:: ከሆነማ ይሁን ብላለች፤ እንዲህ ሆነው ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን በልቶ ጠጥቶ ሰክሮ የመብል የመጠጥ ፈቃዱ ግንኙነት ነውና ልድረስብሽ አላት፤ ምን ብለኸኝ ነበር? አለችው፤ ሴት ብትሆን መቼም ይህን አታደርገውም ወንድም ቢሆን ሳይቀድመን እንቀድመዋለን ብሎ ተገናኛት፤ ይሁዳ ተፀንሶ ተወለደ፤ ሳጥን አበጅቶ ቁልፍ ቆልፎ ከባሕር ጣለው፤ ባሕሩም ወስዶ በአሕዛብ ሀገር ተፋው:: በዚያች ሀገር አንድ

ባለጠጋ አለ አሻግሮ አይቶ ዛሬ ነጋድያንን ማዕበል ሞገድ ቀምቷቸዋል ወርቅ ብር ይኖርበት ይሆናል ብሎ አውጥቶ ከፍቶ ቢያይ ልጅ ነው። ይህንስ አሳድጌ ልጄ አደርገዋለሁ ብሎ ወስዶ አሳደገው ምሑረ ፀብፅ ሰልፈኛ ጦረኛ ሆነ። ይሁዳ ያደገበትና እናት አባቱ ያሉበት ሀገር ፀበኞች ነበሩና ከዚያ ይሁዳ አዋጊ ከዚህ አባቱ አዋጊ ሆነው ተሠለፉ። የይሁዳ ሠራዊት ድል አድርገው ሰውን ማርከው ገንዘቡን ዘርፈው ሲሄዱ ይሁዳም ዘምቶ ነበርና አባቱን ገድሎ ሰለበው ዘአቡሁ ዕልገቱ ያለው ተፈጸመ። አባቱን ገድሎ ወደ ሰፈር ሲገባ እናቱን አግኝቶ ማርከ ሄደ። ማታ ልድረስብሽ አላት ተወኝ ኀዘንተኛ ነኝ። ያ የገደልኸው ባሌ ነው አለችው። ለጊዜው ትቷታል ኋላ ግን እሷን ሚስት አድርጎ ተቀመጠ ዘእሙ ብእሲቱ ያለው ተፈጸመ። ከዕለታት አንድ ቀን ምነው በዚህ ሀገር አንተም እኅቴ ስትል እነሱም ወንድሜ ሲሉህ አልሰማሁም ዘመድ የለህም ሀገርህ የት ነው? እስኪ ንገረኝ አለችው። ከባሕር ወድቀህ የተገኘህ ነህ ይሉኛል አላት። ደነገጠች ለካ አንተ ርጉመ ነህ ያ የገደልኸው አባትህ ነው እኔም እናትህ ነኝ ብላው ነገሩን ከመሠረቱ ጀምራ አስረዳችው። ሰው ከሆኑ እንደ ዕንጨት እንደ ድንጊያ አይደለምና ፈዘዘ ደነገጠ። ምን ይሻለናል? አላት። በገሊላ ተጎድገ ለክ ኃጢአትከ ተጎድገ ለኪ ጎጢአትኪየሚል ነቢይ ተነሥቷልና ሄደን ኃጢአታችንን ለእርሱ ነግረን እናስተሥርይ ብለው ሄደው ለጌታ ነገሩት።እሷን ተጎድገ ለኪ ኃጢአትኪ ኃጢአትሽ ተሠረየልሽ ብሎ ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ቆጥሯታል። እሱንም ተጎድገ ለክ ኃጢአትከ ኃጢአትህ ተሠረየልህ ብሎ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቆጥሮታል። ፍቅረ ንዋይ እንደሚጸናበት አውቆ በጅሮንድነት (ገንዘብ ቤት) ሾሞታል። ማርያም ጎጥእት ይላታል በሦስት መቶ ወቄት ወርቅ የተገዛ ሽቶ ስትቀባው አይቶ ቢያስላው ለእሱ የሚደርሰው ሠላሳ ብር ሆኖ አገኘው። በዚህ ምክንያት ፍቅረ ንዋይ ተስቦ ጌታውን በሠላሳ ብር ሸጦታልና ጎጥእ የጎጥእ ልጅ አለ። ዘእግዚኦ ሴጡ ያለው ተፈጸመ።

ይ.ሕ. ከማሁ።

ሕዝቡም እንደ ቄሱ ይበሉ።

ይ.ዲ. አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት።

ዲያቆኑ ቀሳውስት እጆቻችሁን አንሡ ይበል። ምነው ቄሱ አንድ አይደለም? ስለምን ቀሳውስት ብሎ አበዛ ቢሉ መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማድ ነው በተአምኖ አመ ነገርዎ ለኖኅ ብዕዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምነበ እግዘአብሔር እንዲል። አንድም ንፍቁን ቄስ ጨምሮ ቆጥሮ ነው ሠራዒው ካህን ኅብስቱን አንሥቶ ይይዛል ንፍቁን ቄስ ማኅፈዱን ይገልጥለታል ጽዋውን ያቀርብለታልና። አንድም ሠራኢው ካህን ኅብስትኑ ለማንሣት ንፍቅ ካህን ማኅፈዱን ለማንሣት እጆቻችሁን አንሡ ይበል። በከመ አንጻሕኩ እስኪል ድረስ ማኅፈዱ እንደተሸፈነ ይቆያል፤ ዘኮነ ንጹሐ ብሎ ታጥቦ ሲመለስ ንፍቁ ቄስ ማኅፈዱን ይገልጥለታል። ማንሣቱ የትንሣኤ ምሳሌ፤ አንሥኡተ ማኅፈድ መልአክ ወአንከርከራ ያላት የድንጋይቱ ምሳሌ፤ ግልጸተ ማኅፈድ ወሰበን ዘዲበ ርእሱ እንተ ባቲ ጥብሉለ ያለው የሰበኑ ምሳሌ፤ ሕዝቡ ነአምን ማለታቸው ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ሲገንዙት በመለኮታዊ ሕይወት ሕያው እንደሆነ ለማጠየቅ፤ ዓይኑን ግልጥልጥ ቢያደርግባቸው መለኮቱን ለማስረዳት እንደሆነ አውቀዋልና የዚያ ምሳሌ ነው።

ይ.ሕ. ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

ሕዝቡም በእውነት ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ይህ እንደሆነ በእውነት እናምናለን። አንድም ካህኑ ኅብስቱን ማንሣቱ የትንሣኤ ምሳሌ መሆኑን እናምናለን ይበሉ።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

አሜሃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነሥአ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት ወንጹሓት እለ እንበለ ርስሐት ወነውር።

አሜሃ በዕለተ ኀሙስ ነው፤ አደፍ ጉድፍ የሌለባቸው ንጹሓት ክቡራት በሚሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንሥቶ፤

አንቃዕደወ ሰማየ ኀበ አቡሁ።

ወደ ሰማይ አባቱ አመለከተ፤ ይህን ኅብስት የማበረክትበት ሥልጣን ካንተ ጋራ አንድ ነው ሲል፤ አንድም ለአብነት ተአምራት ይደረግልን

ጥቂቱ ይበርክትልን ባላችሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር አመልክቱ ለማለት። አሜሃ ሲል ያነሣዋል መልሶ ያኖረዋል፤ እግዚኦ ሲል ያነሣዋል መልሶ ያኖረዋል፤ እግዚኦ ሲል ያነሣዋል መልሶ ያኖረዋል፤ አሜሃ ሲል ማንሣቱ የትንሣኤ፤ መልሶ ማኖሩ አርባ ቀን የማስተማሩ፤ እግዚኦ ሲል ማንሣቱ የዕርገት፤ መልሶ ማኖሩ የዳግም ምጽአት ምሳሌ።

ወአስተምሐረ ወላዲሁ።

የባሕርይ አባቱን አደራ አለ።

ወአማኅፀነ አርዳኢሁ።

ደቀ መዛሙርቱን ሰማይ ሩቅ አደራ ጥብቅ ብሎ አስጠበቀ።

ከመ ይዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ።

ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ይጠብቃቸው ዘንድ፤

ባረከ እንዘ ቡሩክ ውእቱ።

የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ አከበረ ለወጠ፤

ፈተተ እንዘ ቅዱስ ወእቱ።

ክቡር ልዩ እንደ መሆኑ ገመሰ ቆረሰ፤ አንድም ዐሥራ ሦስት አደረገ በጌዴዎን ልማድ ዐሥራ ሦስት ሆኖ ሠውቶ ነበርና። አንድም ለአብነት አንዱን እሱ የሚቀበለው ነውና። አንድም ዝ ውእቱ ሥጋየ ወዝ ውእቱ ደምየ ባላቸው ጊዜ ትኩስ ሥጋ ትኩስ ደም ሁኗልና እንዳይገረሙ ቀምሶ ለማቅመስ፤ ጥሒሞ አጥዐሞሙ እንዲል እንደ ባለመድኃኒት ያ ቀምሶ እንዲያቀምስ ጌታም ተቀብሎ አቀብሏቸዋል፤ አቀብሎ ባይቀበል ኖሮ ዛሬ ሠራዒው ቂስ ሳልቀበል አቀብዬ ልሂድ ባለ ነበርና ለአብነት፤ አንድም ነገ ዐሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል እቀበላለሁ ሲል። እነዚህም አክሊለ ሦክ፣ ተኮርያተ ርእስ፣ ተጸፍኦ መልታሕት፣ ወሪቀ ምራቅ፣ ሰትየ ሐሞት፣ ተአሥሮ ድኅሪት፣ ተቀሥፎ ዘባን፣ ርግዘተ ገቦ፣ ርግዘተ ገቦስ ከሞተ በኋላ ነው አይሰማውም ብሎ ጸዊረ መስቀል፣ አምስቱ ቅንዋት ናቸው። አምስቱ ቅንዋት የሚባሉት ሁለቱ ቅንዋት ቀኝ እጁና ግራ እጁ ላይ፣ ሁለቱ እግሩን ደርበው በአንድ ቀኖት ቸንክረውታል፤ አንዱ ከደረቱ ላይ ይህስ ኢትስብሩ አፅሞ ለበግዕ ያለው ይፈርሳል ብሎ እግሩን እየራሱ

ቸንክረውታል ቢሉ የተመቸ፤ አንድ ላይ ነው ቢሉ ስቁረቱን ያያል፤ አንዱ ከመስቀሉ አኖት ላይ ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ ብለው ጠርቀው የያዙበት ነው ይህስ ምን አገናኘው ቢሉ መዘባበት መከራ ነውና።የመስቀሉን አግድመት የያዙበትን የሚቆጥሩም አሉ። ስማቸውም ሳዶር፤ አላዶር፤ ዳናት፤ አዬራ፤ ሮዳስ ይባላሉ።

ወወሀቦሙ ለእለአሁ አርዳኢሁ።

ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው።

ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ጎብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትወሀብ ለቤዛ ኩሉ ዓለም።

ስለ ሁሉ ቤዛና ስለእናንተ ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚፈተት ሥጋየ ይህ ነውና እንኩ ብሉ አላቸው። እማሬ ያለበት ነው፤ ሕንክመ ይላል አክብሮ እንደ ሰጣቸው አክብረው እንደተቀበሉ ለማጠየቅ፤ ጎብስቱን ዘባናኑን ሳይለይ ቀስ ቀስ ብሎ ከአምስት ላይ ወጋ ወጋ ያደርገዋል ያነቃዋል ከላይ ከታች ከቀኝ ከግራ ከጎኑ አምስት ይሆናል፤ አምስቱ የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ፤ አንድም የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ነው፤ አንድም ዐራቱ የአራቱ ቅንዋት አንዱ የኵናተ ሐራዊ ምሳሌ።

ይሕ. አሜን አሜን አሜን።

ሕዝቡም እውነት ነው ይገባል ይበሉ፤

ነአምን ወንትአመን።

በነፍስ በሥጋ ለጊዜውም ለዘለዓለሙም ፈጽመን እናምናለን።

ንሴብሐከ አ እግዚእነ ወአምላክነ።

አቤቱ ፈጣሪያችን ጌታችን አምላካችን ሆይ እናመሰግንሃለን።

ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

ይህ ሥጋህ እንደሆነ በእውነት እናምናለን። አንድም ይህ ሥጋህ እንደሆነ አምነን እናመሰግንሃለን። ሦስት ጊዜ አሜን አሜን አሜን አለ የሦስትነት ቃሉ ያለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ፤ አንድም በደማዊት ነፍስ፤ በነባቢት ነፍስ፤ በሥጋ እንቀበላለንና በዚህ እንደካሠልን ለማጠየቅ።

Scanned by CamScanner

ይ.ካ.

ይበል ካህን፡፡

ወከማሁ ጽዋዐኒ እምድኅረ ተደሩ አንጻረ፡፡

በግዐ ፍሥሑን ከተመገቡ በኋላ በእናንተ ምክንያት ለዓለም ሁሉ ድኅነት ሆኖ የሚሰጥ አንድም እናንተን አብነት አድርገው ለሚቀበሉት ሁሉ ድኅነት ሆኖ የሚሰጥ ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚሠዋው ሥጋዬ ይህ ነውና እንካችሁ ብሉ ብሎ ሥጋውን ሰጣቸው፡፡ ይህንስ መብልዕ ዘአሠርቱ ምእት ዓመት ይለዋል ብሎ ሥጋውን ከሰጣቸው በኋላ ደሙን ሰጣቸው፡፡

ወይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ያነቅዖ ኵናት፡፡

ስለናንተ ነገ በመልዕልተ መስቀል ኵናተ ሐራዊ የሚያፈሰው ደሜ ይህ ነውና እንኩ ጠጡ አላቸው፡፡ ድማሬ ያለበት ነው ያነቅዖ ባለው ይነክንኮ ይላል፤ የአይሁድ ጭፍራ ሞተ ወይስ አለ? ብሎ ጎኑን ወግቶ ሲነቅለው የጌታ ሰውነቱ ተነዋውጧል፤ ዛሬም ቄሱ በቀኝ አውራጣቱ የጽዋውን ከንፈር ይዞ ይወዘውዘዋል ጌታዬ እንዲህ ተነዋውጠህ ነበር ለማለት ነው፡፡ በቀኝ እጁ እንጂ በግራ እጁ ምንም ምን መሥራት አይገባውም፤ ወኢይደልዎ ለካህን ከመ ይልክፍ በእዴሁ ዘጸጋም ከናፍረ ጽዋዕ እንዲል እንዘ ቅዱስ ውእቱ አለ፡፡ ከአትክልት ወይንን፣ ከአዝርእት ስንዴን፣ ከፍጥረት አብርሃምን መረጥኩ ብሎ በዕዝራ እንደተናገረ፡፡ ወእምኵሉ ኦማ ለምድር ኀረይኩ አሐተ ዐጸደ ወይን እንዲል፡፡[121]

ይ.ሕ. አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ፡፡

ትርጓሜው እንዳለፈው፤

ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን፡፡

ይህ ክቡር ደምህ እንደሆነ በእውነት እናምናለን፡፡ አንድም ይህ ደምህ ክቡር እንደሆነ እናምናለን አምነንም እናመሰግንሃለን፡፡

ይ.ካ.፡፡

ይበል ካህን፡፡

---

121 ዕዝራ ሱቱኤል ፫ ፥ ፳፫ ፤ ዕዝራ ሱቱኤል ፰ ፥ ፳፩

ወለዝ ሶበ ትገብርዎ ተዝካረ ሞትየ ትገብሩ::

ነብስቱን በምትለውጡበት ጊዜ፤ አንድም በምትቀድሱበት ጊዜ መታሰቢያዬን አድርጉ፤ አንድም ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የሕማሜን፣ የሞቴን፣ የትንሣኤዬን ነገር ታሰቡታላችሁ፤ መሥዋዕቱ ካለ ዘንድ ሕማሙ ሞቱ የግድ ይታሰባልና:: ትገብሩ ማለቱ እስከ ዕለተ ምጽአት ሲደረግ ይኖራልና አንድም ግበሩ ይላል መታሰቢያዬን በስንዴ በወይን አድርጉ::

ወተዝካረ ትንሣኤየ ትዜንዉ::

ዜንዉ ሲል ነው፤ ንዜኑ ሞተከ ወትንሣኤከ ቅድስተ እያላችሁ አስተምሩ::

ይ.ሕ. ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ::

ሕዝቡም አቤቱ ሞትህን ልዩ የሚሆን ትንሣኤህን ሞተ ተነሣ ብለን እንናገራለን:: ልዩ አለው ትንሣኤውን ከነአልዓዛር ትንሣኤ ሲለይ ነው፤ የነአልዓዛር ትንሣኤ አስነሽ ይሻል፤ እሱ ግን በገዛ ሥልጣኑ ነውና:: ወተንሣእኩ አነ በሥልጣነ ባሕቲትየ እንዲል:: ምነው አብ አንሥኦ መንፈስ ቅዱስ አንሥኦ ይላልሳ ቢሉ አንድ ነው ዕሪናቸውን ለመናገር ነው:: አንድም የነአልአዛር ትንሣኤ ትንሣኤ ዘጉባዔን ይጠብቃል፤ እሱ ግን ፈጥኖ ተነሥቷልና:: ወአኅጸረ ዕድሜ ለርእሱ እንዲል:: አንድም የነአልዓዛር ትንሣኤ ዳግም ሞትን ያስከትላል፤ እሱ ግን ዳግም ሞት የለበትም:: ወኢይረክቦ እምዝ ዳግም ሞት እንዲል:: አንድም የነአልአዛር ትንሣኤ ሞት በሚስማማው በብሉይ ሥጋ ነው የእሱ ግን ሞት በማይስማማው በሐዲስ ሥጋ ነውና::

ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ::

ዕርገትህን ዳግመኛም ዓለምን ለማሳለፍ መምጣትህን እናምናለን::

ንሴብሐከ ወንትአመነከ::

ሞትህን ትንሣኤህን ዕርገትህን ዳግም ምጽአትህን አምነን እናመሰግንሃለን::

ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ::

ጌታችን አምላካችን ሆይ አምነን እያመሰገንህ እንለምንሃለን እንማልድሃለን::

ይካ.

ይበል ካህን።።

አ እግዚአ በከመ አሜሃ ዘንተ ጎብስተ ባርክ ወፈትት ወሀብ።።

አሜሃ በዕለተ ኀሙስ ነው በጎብስቱ ላይ ወደ ጎብስት ያመለክታል፤ በዕለተ ኀሙስ ለሐዋርያት አክብረህ ለውጠህ እንደ ሰጠሃቸው ዛሬም ይህን ጎብስት አክብረህ ለውጠህ ስጣቸው።። አንድም ይህን ጎብስት አክብረህ ለውጠህ የእኔን እጅ እጅ አድርገህ ስጣቸው።።

ይ.ሕ. አሜን።።

ሕዝቡም እውነት ነው ይገባል ይበሉ።።

ይ.ካ..

ይበል ካህን።።

አ እግዚአ በከመ አሜሃ ዘንተ ጽዋዐ ዕተብ ወቀድስ ወመጡ።።

አሜሃ በዕለተ ኀሙስ ነው በጽዋው ላይ ወደ ጽዋው ያመለክታል፤ በዕለተ ኀሙስ ለሐዋርያት አክብረህ ለውጠህ እንደ ሰጠሃቸው ዛሬም ይህን ጽዋ አክብረህ ለውጠህ ስጣቸው።። አንድም ይህን ጎብስት አክብረህ ለውጠህ የእኔን እጅ እጅ አድርገህ ስጣቸው።።

ይ.ሕ. አሜን።።

ሕዝቡም እውነት ነው ይገባል ይበሉ።።

ይ.ካ. ወዘንተ ዘዚአየ ተክህኖ።።

ኀበ ርእሱ ይላል ወደራሱ ያመለክታል ይህን የእኔን ሥልጣን፤

አንጽሕ።።

አንትሙ ንጹሓን እንዳልካቸው እንደ ሐዋርያት አድርግልኝ።።

ወኀረይ።።

አኮ አንትሙ ኀረይክሙኒ አላ አነ ኀረይይኩክሙ እንዳልካቸው እንደ ሐዋርያት አድርግልኝ።።

ወሥመር።።

ሠመርኩ ብክሙ እንዳልካቸው እንደ ሐዋርያት አድርግልኝ።።

Scanned by CamScanner

ይ.ሕ. አሜን።

ሕዝቡም እውነት ነው ይገባል ይበሉ።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

ወዘንተ ካህነ ዘሀሉ ምስሌየ እንዘ ይትራድአኒ በዝንቱ ምሥጢር።

ወደ ካህን ያመለክታል በዚህ በሥጋው በደሙ የሚራዳኝን ይህን ንፍቅ ካህን፤

ረስየኒ ለጢኒ ወለተኒ ከመ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ እለ ገነዝዎ ሥጋከ።

እሱንም እኔንም አንትሙ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ እለ ገነዝክምዎ ለሥጋየ ወአነሂ አዐርፈክሙ ዲበ መንበረ ሶፎር እንዳልኻቸው እንደ ዮሴፍ እንደ ኒቆዲሞስ አድርገን። አይሁድ ጌታን ሰቅለው ከገደሉት በኋላ ዮሴፍ ኒቆዲሞስ የሚባሉ ደጋግ ሰዎች ልቡ ለጻድቅ ውኩል ከመ አንበሳ[122] እንዲል። እሱን ያገኘ መከራ ያገኘናል ሳይሉ ሳይፈሩ በድፍረት ሳይጠራጠሩ በእምነት ከጲላጦስ ተካሠው ከመስቀል አውርደው ልጥስ እንዳይልባቸው በድርብ በአዲስ በፍታ ሲገንዙት ወአንበሰብሰ አዕይንቲሁ እግዚእ ኢየሱስ እንዲል ዐይኖቹን ግልጥልጥ አድርጎ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እያላችሁ ገንዙኝ እንጂ እንደ ዕሩቅ ብእሲ ለምን ዝም ብላችሁ ትገንዙኛላችሁ ብሏቸው ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማትሞት የማትለወጥ እያሉ ገንዘውታል፤ ወዲያው አ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ በከመ አክበርክሙኒ ወሰዐምክሙኒ ወገነዝክሙ ሥጋየ በሰንዱናት ከማሁ አነኒ አከብረክሙ ወእስዕመክሙ ወአነብረክሙ ዲበ መንበረ ሶፎር ሰማያዊ ብሏቸዋል።

ይ.ሕ. አሜን

ሕዝቡም እውነት ነው ይገባል ይበሉ።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

---

[122] ጻድቅ እንደ አንበሳ ያለፍርሃት ይኖራል። ምሳሌ ፳፰ ፥ ፩

ወዘንተ ዲያቆን ዘተልእከ በከመ ሕገ ላእክ አብጽሖ ካዕበ ነበ ዘየዐቢ መዐርገ ሚመጥ ክህነት እንቲአነ።

ነበ ዲያቆን ይላል ወደ ዲያቆኑ ያመለክታል እንደ እስጢፋኖስ የሚያገለግል ይህን ዲያቆን ከማዕርገ ዲቁና ወደ ማዕርገ ቅስና አብቃው።

ወረሰዮ ምሉአ ጸጋ ወጽድቅ ወሞገስ ከመ እስጢፋኖስ ዘርእየ ነሉና ሥላሴ ዘበላዕሉ አንክረ ውተፋጸየ በርደተ መንፈስ ቅዱስ።

መንፈስ ቅዱስ አድሮበት የሥላሴን አኗኗር አይቶ እንደ አደነቀ እንደ እስጢፋኖስ ይህን ዲያቆን ጸጋን እውነትን ክብርን የተመላ አድርገው። እስጢፋኖስ ሀገረ ሙላዱ ኢየሩሳሌም ነው። አባቱ ስምዖን እናቱ ሐና ይባላሉ። ቤተሰቦቹ ቅዱሳንን ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡ ደጋጎች ነበሩ። እስጢፋኖስ ፍጹም እምነት፣ መንፈሳዊ ቅናት የነበረው፣ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት፣ ጥበብና ማስተዋል የተሞላ ቅዱስ ሰው ነው። ሐዋርያት የትምህርተ ወንጌል፣ የጸሎትንና የአስተዳደርን ሥራ በየመልኩ ሥርዓት ባስያዙ ጊዜ በመልካም ሥራ ከተመሰከረላቸውና መንፈስ ቅዱስ ከሞላባቸው ሰባት ዲያቆናት አንዱ ሆኖ በበላይነት ለአገልግሎት ተመርጦ በሐዋርያት አንበሮተ ዕድ ተሾሟል። እስጢፋኖስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳንና በነቢያት የተነገረውን እየጠቀሰ ሲያስረዳቸውና ምላሽ ሲያሳጣቸው አይሁድ በቅንአት መንፈስ ተነሣስተው በድንጋይ በወገሩት ጊዜ እነሆ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦለት ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይ አባቱ በአብ ቀኝ ተቀምጦ አይቷል። ወርኢኩ ርኁወ ሰማየ ወኢየሱስ ይነብር በየማኑ እንዲል።[123] አንድም ይትፋጸይ ይላል ያድንቅ ሲል ነው።

ይ.ሕ. አሜን።

እውነት ነው ይገባል ይበሉ። አምስት ጊዜ አሜን አለ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር አንድም የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ ነው።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

---

123 የሐዋርያት ሥራ ፯ ፥ ፶፮።

ወለእሉ ሕዝበክ እለ ተጋብኡ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ምስለ ካህናት ወዲያቆናት።

ከቀሳውስት ከዲያቆናት ጋራ በቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡ እሊህን ሕዝብ፤

ዐቢየ ወንዑሰ።

ትልቁንም ትንሹም፤

አድሉ ለነፂአ ምሥጢርክ ቅዱስ።

ሥጋህን ደምህን ለመቀበል አብቃ።

መሐር ወኢትስኪ።

ይቅር በላቸው እንጂ አትፍረድባቸው።

ይ.ሕ. አሜን እግዚኦ መሐረነ።

እውነት ነው ይገባል ይበሉ። አንድም በእውነት ይቅር ልትለን ይገባል።

እግዚኦ መሐክነ እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ በእውነት እዘንልን ራራልን።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ የተናገረው ፈያታይ ዘየማን ነው። ደግ ጸሎት ነውና ብሎ ከሥርዐተ ቅዳሴ አምጥቶ ተናግሮታል። አንድም እሱ ተናግሮታል ሰው ሞቶ ይህን ጸልዮ አስነሥቶበታል። በዐቢይ ሦስት በንዑስ ሦስት ስድስት ይሆናል የስድስቱ ቃላተ ወንጌል አንድም አምስቱ የአምስቱ ቅንዋት አንዱ የሱናተ ሐራዊ ምሳሌ።

ይ.ዲ.።

ይበል ዲያቆን።

በሙሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ጎበረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ።

በመንፈስ ቅዱስ አንድ መሆንን ይሰጠን ዘንድ፤ አንድም ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ ያደርገን ዘንድ በፍጹም ልቡናችን ፈጣሪያችን

እግዘኢብሔርን እንለምነው። አንድነታችን ከእርሱ ጋራ ነው፤ አንድም እርስ በርሳችን ነው።

ይ.ሕ. በአመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ።

በቅድምና የነበረ ዛሬም ያለ ወደ ፊትም ዓለምን አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖር እሱ ነው።

ይ.ካ. ደሚረክ ህበመ ለዙሎመ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ።

በመንፈስ ቅዱስ አንድ አድርገህ ትሰጣቸው ዘንድ አደሉ ላለው።

ይኩኖመ ለሕይወት ዘለዓለም።

ያው ለዘለዓለም መድኃኒት ሊሆናቸው አንድም ህበመ ያው ራሱ ለዘለዓለመ ሕይወት መድኃኒት ይሆናቸው ዘንድ ሥጋውን ደሙን ስጣቸው። አንድም ሥጋውን ደሙን ስጣቸው ያው ለዘለዓለመ ሕይወት መድኃኒት ይሁናቸው።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

ህበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ።

ባንተ ህልውና ባለ መንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ አንድ መሆንን ስጠን።

ወፈውሰነ በዝንተ ጽርስፎራ።

በዚህ በቅዱስ ሥጋው ከደዌ ነፍስ ከደዌ ሥጋ አድነህ ፈውስ ሥጋን ፈውሰ ነፍስን ስጠን።

ከመ ብከ ንሕየው።

ባንተ ሕያውነት ሕያዋን ሆነን እንኖር ዘንድ። አንድም ቡቱ ይላል በዚህ በሥጋው እንከብር ዘንድ መክበሩን ስጠን።

ዘለኩሉ ዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ለዘለዓለመ ሕያዋን ሆነን እንኖር ዘንድ።

ይ.ሕ. ከማሁ።

ሕዝቡም እንደ ቁሱ ይበሉ።

Scanned by CamScanner

ይ.ካ. ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር፡፡

ካህኑም እግዚአብሔር አብ ክቡር ምስጉን ነው ይበል፡፡ ቡሩክ አለ ብሩክ አብርሃም ያመሰግነው ነበርና፡፡

ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር፡፡

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ምስጉን ነው፡፡ አንድም አቡየ ፈነወኒ ወአነ ተፈኖኩ ብሎ የሚመጣ ምስጉን ነው፡፡ አንድም እግዚአብሔር ነኝ ብሎ የሚመጣ ምስጉን ነው፡፡ አንድም እግዚአብሔር ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ መስክሮለት የሚመጣ እግዚአብሔር ወልድ ክቡር ምስጉን ነው፡፡ አንድም መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን የሚያርቅ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል ምስጉን የባሕርይ አምላክ ነው፡፡

ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ፡፡

መንፈስ ቅዱስም ክቡር ምስጉን ነው፡፡

ለይኩን ቡሩከ ለይኩን፡፡

ይሁን ይሁን ይጽና ይደረግ፡፡ ሦስት ጊዜ ለይኩን አለ ቡሩክ ስሙ ብሎ ለአብ ሰጥቶ ነበርና ለይኩን፤ ወቡሩክ ዘይመጽእ ብሎ ለወልድ ሰጥቶ ነበርና ለይኩን፤ ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ብሎ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ነበርና ቡሩከ ለይኩን አለ፤ ዕሪናቸውን ለመናገር ነው፡፡

ይ.ሕ. ከማሁ፡፡

ሕዝቡም እንደ ቄሱ ይበሉ፡፡

ይ.ካ. ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ፡፡

ካህኑም በሥጋው በደሙ ምክንያት መንፈስ ቅዱስን አሳድርብን ይበል፡፡ አንድም በሥጋው በደሙ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም አድሮብን ይኑር፡፡

ይ.ዲ. ተንሥኡ ለጸሎት፡፡

ዲያቆኑ ለጸሎት ተነሡ ይበል፡፡

ይ.ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፡፡

ሕዝቡም አቤቱ በነፍስ በሥጋ ይቅር በለን ይበሉ፡፡

ይ.ካ. ሰላም ለኵልክሙ፡፡

ካህኑ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ይበል፡፡

ይ.ሕ. ምስለ መንፈስከ፡፡

ሕዝቡም ከመንፈስህ ጋራ ይበሉ፡፡ ወብነ አሐዱ መንፈስ ዘሃይማኖት እንዲል አንድም ቃልህ አይለየን ይጽናልን ይበሉ፡፡ ተንሥኡ ለጸሎትን በዲያቆኑ ተገብቶ የተናገረው አዳም ነው ጌታ በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ብሎት ተስፋውን ነግሮት ነበርና ቀረን? እያለ ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ጌታ በዕለተ ዐርብ በአካለ ነፍስ በዐሥራ አንድ ሰዓት ወደ ሲኦል ወርዶ ብርሃነ መለኮቱን ቢነዛላቸው አዳም ተንሥኡ ለጸሎት ብሏቸዋል እነሱም አቤቱ ይቅር በለን ብለዋል ጌታም ሰላም ለኵልክሙ ሰላም ለእናንተ ይሁን እንዴት ሰነበታችሁ ታረቅኂችሁ አስታረቅኂችሁ መስቀል ቀረላችሁ ይላቸዋል ምስለ መንፈስከ እንደ ቃልህ ይደረግልን ብለዋል፡፡